## በFCPS መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሳይንስ ደህንነት/ጥንቃቄ ስምምነት።

ሳይንስ በእጅ እየተነካ የሚተገበር የቤተ ሙከራ ምርምር የትምህርት ክፍለግዜ ነው። አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎችን፣ ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን በእጅ መንካትን የሚጠይቁ የቤተ ሙከራ ምርምሮችን ታደርጋላችሁ። በሳይንስ ክፍል የተማሪዎች፣ የአስተማሪዎች እና የቤተሰቦች ደህንነት ቁጥር አንድ ቅድሚያ የሚሰጠው ትኩረት ነው። በሳይንስ ክፍለ ጊዜ ደህንነትን ለማረጋገጥ ሲባል በተማሪዎች ደህንነት ስምምነት ውስጥ የተለያዩ ዝርዝር ሕጎች ተካተዋል። በማንኛውም ሰዓት ሕጎችን መከተል ግዴታ ነው። የስምምነቱ ሁለት ቅጂዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል። በሳይንስ ቤተሙከራ ከመሳተፋችሁ በፊት ስምምነቱ በቤተሰብ ወይም በአሳዳጊ እና በእናንተ መፈረም ይኖርበታል። ሁለተኛው ቅጂ በሳይንስ ማስታወሻ ደብተር ውስጥ እንደ ቋሚ የደህንነት ሕጎች ማስታወሻ ሆኖ ይቀመጣል።

### አጠቃላይ

1. ሁሉንም መመሪያዎች እና አቅጣጫዎች በጥንቃቄ ተከተሉ። በቤተ ሙከራ ውስጥ ምንም አይነት ምርምር ከማድረጋችሁ በፊት ሁሉንም ምልክቶች እና የመሳርያዎቹን አጠቃቀም አንብቡ።
2. ሁልጊዜ በቤተ ሙከራ ውስጥ በኃላፊነት ተንቀሳቀሱ። በቤተ ሙከራ ውስጥ አትረብሹ እንዲሁም አትቀልዱ።
3. በቤተ ሙከራ ውስጥ መብላት ወይም መጠጣት አይቻልም።
4. ተቆጣጣሪ በሌለበት በቤተ ሙከራ ውስጥ በፍፁም ስራ እንዳትሰሩ።
5. ካልታዘዛቹ በስተቀር ማንኛውንም የቤተሙከራ መሳሪያ ወይም ቁሳቁስ መንካት አይቻልም።
6. ያልተፈቀደ ሙከራ ማድረግ ክልክል ነው። ያለ አስተማሪ ፈቃድ በስተቀረ የሙከራ ሂደቱን እንዳትቀይሩ።
7. ምርምር የሚካሄድበትን ቦታ ከምርምሩ በፊት፣ ምርምሩን እየተተገበረ እያለ እንዲሁም ከተተገበረ በኋላም አታዝረክርኩ ንፅህናውንም ጠብቁ።
8. በቤተ ሙከራ ውስጥ ምርምር እያካሄዳችሁ አይናችሁን፣ አፍንጫችሁን እና አፋችሁን ከመንካት ተቆጠቡ/አትንኩ።
9. ሁሉንም በቤተሙከራ ውስጥ የሚገኙትን የደህንነት መሳሪያዎች የት እንደሚቀመጡ እና አጠቃቀማቸውን እወቁ።
10. በቤተ ሙከራ ውስጥ ምናልባት አስጊ የሆነ ነገር ከተመለከታችሁ ወዲያውኑ ለአስተማሪያችሁ አሳውቁ።
11. ሁሉንም ከቤተ ሙከራው ክፍል የሚወጣውን ቆሻሻ በመምሪያው መሰረት አስተናግዱ/አስወግዱ።
12. እንደየአስፈላጊነቱ ቤተ ሙከራ ክፍሉን ከመልቀቃችሁ በፊት እጃችሁን በሳሙና እና ውሃ ታጠቡ።
13. ከአስተማሪያችሁ ፈቃድ ሳታገኙ ወደ ቤተሙከራ ክፍል ወይም መጋዘን አትግቡ።
14. የእሳት አደጋ ጊዜን ደወል ወይም ሌሎች የቤተሙከራን መቋረጥ የሚያሳውቁ ምልክቶች ሲከሰቱ የሚገሉ ነገሮችን አጥፉ፣ ሁሉንም የዕቃ መያዣዎች/ማስቀመጫዎች ዝጉ እና በጋዝ የሚሰሩ መሳሪያዎችን አጥፉ።
15. በቤተ ሙከራ ውስጥ ስለታማ ነገሮችን በጥንቃቄ ተጠቀሙ። ሁልግዜ ስለታማ ነገሮችን በእጀታቸው/በመያዣቸው በኩል በመያዝ እና ስለቱን ከናንተ እና ከሌሎች ሰዎች በተለየ/ተቃራኒ አቅጣጫ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።
16. በቤተ ሙከራ ውስጥ ለመስራት እንዳትችሉ የሚያውካችሁ ምንም አይነት የጤና ችግሮች ካጋጠሟችሁ ወዲያውኑ ለአስተማሪያቹ አሳውቁ። የጤና ችግር ካለባችሁ በቤተ ሙከራ ውስጥ ስራ ከመስራታችሁ በፊት ሁልግዜ ሃኪም አነጋግሩ።

### አለባበስ እና ራስን የመከላከያ/ደህንነት መሳሪያዎች

17. ሁልጊዜ የአይን መከላከያ መነፅር ማድረግ አለባችሁ። ንጥረ ነገሮችን/ኬሚካሎችን፣ የጋሉ ነገሮችን እና ተሰባሪ ቁሳቁሶችን/ጠርሙሶችን ስትጠቀሙ
18. በቤተ ሙከራ በሚትሳተፉበት ጊዜ በስነስርዓቱ መልበስ ይኖርባችኋል።(ከበታች ተመልከቱ)

### አደጋ እና የመቁሰል/የአካል መጎዳት

19. ሁሉንም አይነት አደጋዎች፣ የአካል ጉዳቶች ወይም የንጥረነገሮች/የኬሚካሎች መፍሰስ ሲከሰቱ ለሚመለከተው ክፍል በፍጥነት አሳውቁ/ንገሩ።

### የንጥረነገሮች/የኬሚካሎች አያያዝ

20. ረዥም ፀጉር፣ የተንዘላዘለ ልብስ እና ጌጣጌጥ ወደ ኋላ መደረግ/መታሰር አለበት። አውራጣት የማያሳይ ሽፍን ጫማ መጫመት/ማድረግ ያስፈልጋል።
21. ከቤተ ሙከራ ስራ በኋላ ሲፀዳ:-
    a. ሙከራ ያካሄዳቹበትን ቦታዎች አፅዱ።
    b. የንጥረ ነገሮች/የኬሚካሎች ተዋፅኦዎች/ዝቃጮች በመመሪያው መሰረት መወገድ አለባቸው።
    c. እጃችሁን በሳሙና እና ውሃ ታጠቡ።
22. ምንም አይነት ንጥረነገር/ኬሚካል አትቅመሱ አትንኩ። ንጥረነገር/ኬሚካል እንድታሸቱ ከታዘዛችሁ ከመያዣ ውስጥ አየሩን/ትነቱን አስወጡት/አስተንፍሱት። በየትኛውም አይነት መያዣ ውስጥ ያሉ ንጥረነገር/ኬሚካሎችን አታሽትቱ።
23. ብልቃጦችን ለመሙላት የጎማ ቱቦ ወይም መንፊያ ብቻ ተጠቀሙ። በፍፁም አፋችሁን አትጠቀሙ።
24. የሙከራ ብልቃጦችን ከላይ በኩል ሳይሆን በጎን በኩል ተመልከቱ። በሙከራ ብልቃት ውስጥ ንጥረ ነገሮችን/ኬሚካሎችን ለመቀላቀል አስተማርሪያችሁ ያሳያችሁን/ያሳየቻችሁን መንገድ ተከተሉ።
25. ፍሳሾች በደንብ መፅዳት አለባቸው። ፍሳሽ በሚኖርበት ጊዜ ወድያውኑ ለአስተማሪያችሁ አሳውቁ።
26. አሲድ እና ቤዝ በጥንቃቄ መያዝ ይኖርባቸዋል። አሲድ በምታቀጥኑበት ጊዜ ሁልጊዜ አሲዱን ወደ ውሃው ቅዱ/ጨምሩ።
27. ቁስል/ወይም የአካል ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ ወድያውኑ ለአስተማሪው/ዋ አሳውቁ።
28. ንጥረ ነገር/ኬሚካል ወደ ቆዳችሁ በሚገባበት ጊዜ ውሃ ውስጥ ንከሩት።
29. ኬሚካል አይናችሁ ውስጥ ከተረጨ ወደ አይን ማጠቢያ ቦታ በመሄድ ለ20 ደቂቃ ያክል አይናችሁን በውሃ

እርጩት::  አይን ውስት የሚገባ መነፅር/ኮንታክት ሌንሰ ካላችሁ ወድያውኑ አውልቁት::

30. በየጠርሙሶቹ/ብልቃቶች ላይ የተለጠፉትን ምልክቶች እና ፅሁፎች በጥንቃቄ አንብቡ::  ሁልጊዜ ትክክለኛውን ንጥረ ነገር/ኬሚካል መምረጣችሁን አረጋግጡ:: የተለጠፈ ምልክት/ፅሁፍ የሌለበት ንጥረ ነገር/ኬሚካል ሲገኝ ለአስተማሪ አሳውቁ::

**የብልቃቶች/ጠርሙሶች አያያዝ**

31. ሁልጊዜ ብልቃቶችን/ጠርሙሶችን ከመጠቀማችሁ በፊት አለመሰንጠቃቸውን ወይም ስብርባሪ አለመኖሩን አረጋግጡ::  የተሰበረ ብልቃጥ ወይም ጠርሙስ በፍፁም አትጠቀሙ::
32. ማንኛውንም የተሰበረ ወይም የተሰነጠቀ ብልቃጥ ወይም ጠርሙስ ካገኛችሁ ለአስተማሪያችሁ አሳውቁ:: የተሰበሩ ጠርሙሶች በመመሪያው መሰረት መወገድ አለባቸው::

**በገላጣው የሚነድ እሳትን መጠቀም እና ማሞቅ**

33. ረዥም ፀጉር፣ የተንዘላዘለ ልብስ እና ጌጣጌጥ ገላጣ እሳት ወይም የጋለ ነገርን ከመጠቀማችሁ በፊት ወደ ኋላ መታሰር/መደረግ አልባቸው::
34. ገላጣ እሳት ወይም ማንኛውንም የጋለ ነገር ጠባቂ በሌለበት በፍፁም ትታችሁ አትሂዱ::
35. ሁልጊዜ  በእሳት ስትጠቀሙ አትኩሮት እና ክትትል ማድረግ ይኖርባችኋል:: ወደ ገላጣ እሳት በፍፁም አትጠጉ::
36. ጠርሙሶች/ብልቃጦች እና ብረቶች ከጋሉ በኋላ ለረዥም ጊዜ ሳይበርዱ ይቆያሉ እንዲሁም ቀዝቃዛ መስለው ይታያሉ:: ስለዚህ ከመንካታችሁ በፊት እስኪበርዱ ድረስ መከላከያ ባለው ቦታ ላይ አስቀምጧቸው::
37. የጋለ ሳህን በምትጠቀሙበት ጊዜ የጋለውን ቦታ አትንኩት::
38. ስትጨርሱ የጋለውን ሳህን ነቅላችሁ እንዲበርድ ወደ አንድ ጎን አስቀምጡት::
39. በግለቱ ምክንያት ከተቃጠላችሁ/ወይም የአካል ጉዳት ከደረሰባችሁ ወድያውኑ ለአስተማሪያችሁ አሳውቁ::
    a. ቃጠሎ የደረሰባችሁን ቦታ በቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ በመንከር አብርዱ::

**በኤሌክትሪክ የሚሰሩ እና ሌሎች መገልገያዎች/መሳሪያዎች አያያዝ**

40. ሁልጊዜ አንድን በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሳሪያ ገመዱን ሳይሆን መሰኪያውን በመያዝ ንቀሉ:: የኤሌክትሪክ ማብሪያ/ማጥፊያ እና መሰኪያ ስትነኩ እጃችሁ ደረቅ መሆኑን አረጋግጡ::
41. መሳሪያዎችን በግድግዳ መሰኪያ ላይ ከመሰካታችሁ በፊት በዓይናችሁ ፈትሹ እና አረጋግጡ::  ሽቦው የተቃጠለ፣ ወደ ውጭ በተጋለጠ ወይም የላላ መሳሪያ/መገልገያ በፍፁም አትጠቀሙ::
42. የተበላሹ መሳሪያዎች/መገልገያዎች ካሉ ወድያውኑ ለአስተማሪያችሁ አሳውቁ::
43. በቤተ ሙከራ ውስጥ ያሉትን ስለታማ መሳሪያዎች/መገልገያዎች በሙሉ ያሉበትን እወቁ እና በጥንቃቄ ተጠቀሙ::
44. ሁልግዜ ከባድ የሆኑ ዕቃዎችን በጥንቃቄ ያዙ::
45. ጨረራማ ነገሮችን በቀጥታ አትመልከቱ ወደሌላ ሰውም አቅጣጫ አታንፀባርቁ::

**የስነፍጥረት ነክ /የባዮሎጂ ነክ መገልገያዎችን/መሳሪያዎችን አያያዝ**

46. ከጠርሙስ ወይም ከላስቲክ የተሰሩ የቤተሙከራ ጎድጓዳ ሳህኖችን ለመጠቀም/ለማዘጋጀት የአይን መከላከያ መነፅር ማድረግ አለባችሁ::  የአይን መከላከያ መነፅር ምናልባት ናሙናዎችን ለማየት ሲባል ብቻ ለጊዜው ማውለቅ ይቻልላል:: ነገር ግን የባዮሎጂ/ስነፍጥረት ነክ ንጥረ ነገሮችን ስትጠቀሙ በሁሉብ ጊዜ የአይን መከላከያ መነፅር መደረግ ይኖርበታል::
47. ታግቶ/ተጠብቆ የተቀመጠን ናሙና ለመንካት የእጅ ጓንት ማድረግ ይጠበቃል::
48. ታግተው/ተጠብቀው የተቀመጡ ወይም ሂወት ያላቸውን ናሙናዎችን ተጠቀማችሁ ሙከራ ካደረጋችሁ በኋላ ሁሉንም የስራ ቦታዎች አፅዱ እና እጃችሁን በውሃ እና በሳሙና ታጠቡ::

**የተማሪ ስምምነት**

ሁሉንም በዚህ ስምምነት ውስጥ ያሉትን የደህንነት ሕጎች ለመከተል ተስማምቻለሁ:: እነዚህን ሕጎች የመከተል፣ የራሴን እና የሌሎችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለብኝ አውቃለሁ::  ደህንነቱ የተጠበቀ የቤተ ሙከራ አካባቢ እንዲኖር ከአስተማሪዎቼ እና ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በጋራ እሰራለሁ::  በአስተማሪዎቼ የሚሰጡትን የቃል እና የፅሁፍ መመሪያዎችን እከተላለሁ:: የትኛውንም የቤተ ሙከራውን የደህንነት ሕግ/መመሪያ መጣስ እና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ድርጊት መሳተፍ/መፈፀም ለሚከተሉት ነገር ግን በዚህ ላልተወሰኑት የስነስርዓት እርምጃ መወሰድ እንደሚዳርግ ተገዝቤአለሁ::  የትኛውንም የቤተ ሙከራውን የደህንነት ሕግ/መመሪያ መጣስ እና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ድርጊት መሳተፍ/መፈፀም በተማሪዎች መብት እና ግዴታ (SR&R) መሰረት የስነስርዓት እርምጃ መወሰድ እንደሚዳርግ ተገዝቤአለሁ::

የተማሪ ስም:-________________________

የተማሪ ፊርማ :- __________________________

ቀን፡-      ___________________________

**የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:-**

የደህንነት ሕጉን አንቤአለሁ እንዲሁም ለልጄ ደህንነቱ የተጠበቀ ቤተ ሙከራ እንዲኖር ለማስቻል የተወሰዱትን እርምጃዎች ተገንዝበአለሁ:: ልጄ ይህንን ስምምነት ጠብቆ የቤተ ሙከራ ሕጎቹን እንዲከተል እመራዋለሁ::

የወላጅ/አሳዳጊ ስም:-_______________________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:- __________________________

ቀን፡-_____________________________